# የማህበራዊው ሚዲያ ፀረ-ማህበራዊነት

ዋኘው መዝገቡ 03-14-18

በፖለቲካው አለም የሚደግፉትና የሚቃወሙት መስመር መኖሩ አዲስ አይደለም፡፡ ተቃውሞ ምክንያታዊ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ጭፍንና በገነፈለ ጥላቻ የተሞላ ስሜታዊ ተቃውሞ፤ በጀብደኝነት የተሞላ ወዴት እንደሚሄድና  በሀገር ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ለይቶ የማያውቅ ተቃውሞ፤ እነሱ በውጭ ሀገር ስራቸውን እየሰሩ፤ ዶላራቸውን እያፈሱ በደሀ ሀገር ኢኮኖሚ ስራ አትስሩ፣ የስራ ማቆም አድማ አድርጉ፣ ትምህርት አቁሙ፣ ትራንስፖረት ይቁም የሚል ቀጥተኛ ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ተቃውሞና ተቃዋሚዎች ከሀገሪቱ እውነታ የተፋቱ፤ በእውር ድንብራቸው የሚዛብሩ፤ ወዴት እንደሚሄዱ እንኳ በቅጡ ለይተው የማያውቁ ናቸው፡፡ የእብደት ተቃውሞና እብድ ተቃዋሚዎች ማለት እኚህ ናቸው። በተለይ ከወዲያኛው፤ ከዲያስፖራው መንደር ያሉቱ፡፡

በድሀው ሕዝብ ልጅ ሕይወት የሚነግዱ ሸቃዮች የሚቀሰቁሱት ተቃውሞ፤ በመንጋና ጅምላ እሳቤ የተሞላና የሚነዳ ተቃውሞ፤ በውል የተሰመረ መስመር የሌለው ተቃውሞ፤ ሕዝብና ሀገርን ለከፋ አደጋ አጋልጦ የሚሰጥ የእብደት ተቃውሞ፤ የታየውን ጅምር ለውጥ ተቀብሎ የጎደለውን ለመሙላት በጎ አስተዋጽኦ ማድረግ የተሳነው ተቃውሞ የመጨረሻው ግቡ ጥፋትና ውድመት ነው፡፡

እንደ መንደር እድር በዝተው ሞልተው የተረፉ በአላማ ሳይሆን የፓርቲ መሪ ለመባል ብቻ ከመቶ በላይ የሚቆጠሩ መንጋ ፓርቲዎችን መስርተው በባዶ ሜዳ ሲፈላሰፉ ውለው የሚያመሹ፤የቀለም አብዮት ሲያውጁ ሲያሴሩ ሲያስተባብሩ፤አድማ ሲጠሩ ውለው የሚያድሩ፤ በሌሉበት በማያውቁት የሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ወጣቱን በስሜት እየነዱ ለእሳት የሚማግዱ በተመሳሳይ ሁኔታም በመላው አለም እየዞሩ የእርዳታ እርጥባን ገንዘብ ማሰባሰቢያ የልመና ኮሮጆዋቸውን መሙያ ክቡሩን የሰው ልጅ የመነገጃ ሸቀጥ አድርገው ለግል ጥቅማቸው መክበሪያ የሚነግዱበት ነጋዴ ተቃዋሚዎች ሞልተው የተረፉባት በሕዝብዋ ስም የሚነገድባት ሀገር ነች ኢትዮጵያ፡፡ ችግር መኖሩን ገዢው ፓርቲ አምኖ ተቀብሎ ለመለወጥ ሲሰራ የለም ምንም አይነት ለውጥ አንቀበልም፡፡ የምፈልገው ሀገሪቱ ተተራምሳ ተቃውሳ ማየት ነው የሚል የእብደት ተቃውሞ የትም አያደርስም፡፡ ምንም ለውጥ ቢደረግ ቢመጣ አንቀበልም የሚል ለጥፋት ያሰፈሰፈ ተቃውሞ መጨረሻው አጥፍቶ ጠፊነት ነው፡፡

በሕዝባቸው የበላይነትና ታሪክ ሰሪነት ሳይሆን በነጮች የበላይነት አጥብቀው የሚያምኑ በእነሱም ቡራኬ ቅብአ ቅዱስ ተቀብተው ለመንበረ  ስልጣን እንበቃለን ብለው በአውሮፓ አደባባይ ደጅ የሚጠኑ የሚማጸኑ፤ የኢትዮጵያን ክብርና ታላቅነት ያረከሱ የአድዋን የታላቅነትና የጀግንነት ክብር ያዋረዱ በአሽከርነት ያደሩ አፋሽ አጎንባሽ ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች መቸም ሆነ መቸም ለዚህች ሀገር አይበጁም፡፡

የእብደት ተቃውሞአቸው ደርዝና ፈር የለውም፡፡ በጥላቻ ሰክረው የናወዙ ሀገር ማለት ሕዝብ ሀገር ማለት ሰው ሀገር ማለት ወገን መሆኑን የረሱ ናቸው፡፡ ሕዝብ እንዲተላለቅ የጥፋት መልእክት ሲያሰተላልፉ ውለው የሚያድሩ በስደብ በጸያፍ ቃላት የተካኑ፤ የሞተው ሞቶ የረገፈው ረግፎ ምድሪቱ ባዶ ስትሆን ከአውሮፓ መጥተን ስልጣን እንይዛለን ብለው የሚያስቡ ለሀገርና ለሕዝብ ሰላም ሳይሆን በሕዝብ እልቂትና ደም መፋሰስ ስልጣን እናገኛለን ብለው የሚያስቡ ስግብግቦችም ናቸው፡፡

በሀገር ቤት ሕዝብን ለጥፋት እየቀሰቀሱ ልጆቹን እንዲያጣ እያደረጉት እነሱ አውሮፓ ላይ ተዝናንተው ተቀምጠው መግለጫ የሚሰጡ በባዶ ሜዳ የሚኩራሩ በሌሉበት የሽግግር መንግስት፤የምንትስ ቅብጥርስ ኮሚቴ፤ የአደራ ቦርድ እያሉ በሕዝብና በሀገር ስም የሚነግዱ የሚሸቅሉ ማደሪያቸውን በዚሁ ያደረጉ ለስሙ ዶክተር ፕሮፌሰር ምንትስ ቅብጥርስ የሚል የአካዳሚክ ማእረግ የተሸከሙ በተግባር የሕዝባቸውን ችግር ለመፍታት ቀድሞም ዛሬም ያልቻሉ በስሜታዊነት ሕዝብን ለመንዳት የመንጋ ሁከት ለመፍጠር የሚዳዱ የማስተዋል እሳቤ ያጠራቸው ፍጡሮች ናቸው፡፡

ጽንፈኛው አክራሪ ተቃዋሚ አብዛኛው ለግብጽና ለኤርትራ በተቀጣሪ አሽከርነት ያደረ ተላላኪና ከባእዳን በሚያገኘው የሚሊዮኖች ድጎማ ገንዘቡን በእጅ አዙር ወደሀገር ቤት እየላከ ሁከት ብጥብጥ የስራ ማቆም አድማ ወዘተ እየጠራ ወጣቱን በማወናበድ በሀገሩ ላይ እንዲዘምት የጎሳ ግጭት እንዲቀሰቀስ የዜጎች ሕይወት እንዲጠፋ ንብረት እንዲቃጠል እንዲወድም፤ ስራና ምርት እንዲስተጓጎል በዚህም ሕዝቡ የከፋ ቀውስና ችግር ውስጥ እንዲገባ ተግቶ ቀን ከለሊት እያሰራ ያለ ጸረ ሀገርና ጸረ ሕዝብ የሆነ ጥርቅም ነው፡፡

እንደነዚሀ አይነት የመንጋ አስተሳሰብ ያላቸው በእብደትና በጥላቻ ስካር የናወዙ እኛ ስልጣን ካልያዝን ሀገርም ሕዝብም ይውደም ብለው የደመደሙ ይህንን ቅጥረኛ የሆነውን መና ሕልማቸውን ለማሳካት ሲዛብሩ ውለው የሚያድሩ ሕልመኞች ቢባሉ ከእውነት የራቀ አይደለም፡፡

ዛሬም ኢሕአዴግ ለሀገሪቱ ሰላምና ደህንነት የተፈጠረውንም ችግር ፈትቶ የሕዝብንም ጥያቄ በመመለስ የተረጋጋች ኢትዮጵያን ለመምራት ዛሬም ከነድክመቱ ከነጥፋቱ ከነስህተቱ አንድ ሺህ አንድ ግዜ ተመራጭ ነው:: ያለው አማራጭ ሀገሪቱንና ሰላሟን አስከብሮ ለመዝለቅ ዙሪያዋን ያሰፈሰፈውን በግብጽ በኤርትራ በአልሻባብና በአይሲስ አማካኝነት በኢትዮጵያ ላይ የተጠነሰሰውን ግዙፍ ሴራ ለማምከን ብቸኛው አቅም ያለው ከአደጋ ሊታደጋት የሚችለው አማራጭ ኢሕአዴግ ብቻ ነው:: ያለው ብቸኛ አማራጭ የታዩትን ስህተቶቹን አርሞ የተሻለ ሁኖ ሕዝብን እንዲያገለግል ጥያቄዎቹን እየመለሰ እንዲሄድ ማገዝና መርዳት ብቻ ነው::

ሺህ ቦታ በአላማ በግብ የተበታተኑ እርስ በእርሳቸው እየተባሉ ዘመናትን የገፉ ስመ ብዙ ፖለቲካ ፓርቲዎች ድርጅቶች ሀገሪትዋን ሺህ ቦታ እንዲበጣጥሱዋት የኢትዮጵያ ሕዘብ አይፈቅድም:: እዛው የውጭ ኃይሎች ተላላኪነታቸውን አሽከርነታቸውን ይዘው ሳንቲም እየቃረሙ መኖር ይችላሉ:: እነሱን የሚሰማ በእነሱ የጥፋት ቅስቀሳ የሚደለል ለእነሱ መንጋ እሳቤ የሚገዛ የሀገሩን የቤተሰቡን መፍረስና መበታተን የሕዝብን እልቂት የሚመኝ ዜጋ የለም::

በሀገር ውስጥ የተነሱት የመብቴ ይከበርልኝ ጥያቄዎች የተነሱት በራሱ በሕዝቡ ነው:: አውሮፓም ሆነ አሜሪካ ያሉ ወይንም በሀገር ቤት እንገኛለን የሚሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አልመሩትም:: አላደራጁትም:: በግንባር ሆነው አልታገሉም:: ስለዚህም ሕዝቡ ያነሳቸው ጥያቄዎች በአግባቡ ሲመለሱለት ቸግሮቹ ሲፈቱለት ጉዳዩ መቋጫ ያገኛል:: በሀገር ውደመት በሕዝብ ፈተናና ችግር ውስጥ መውደቅ የፖለቲካ ስልጣን እንይዛለን የሚል ተራ እሳቤ ያላቸው ወፈፌዎች ከዚህ እብደታቸው ቢወጡ ለእነሱም የተሻለ ነው የሚሆነው::

ኢሕአዴግ ሀገሪቱን በመለወጥና በማሳደግ ረገድ እጀግ ስርነቀል ለውጦችን ያስመዘገበ ታሪክን በአዲስ መልክ የጻፈ ሀገሪቱን በኢኮኖሚ አብዮት ወደላቀ ምእራፍ የመራ ግዙፍ የፖለቲካ ድርጅት ነው:: በኖረው ታሪካችን ያልተሰሩ ያልተሞከሩ የማይደፈሩ የተባሉ ድንቅ ስራዎችን የሰራ ድርጅት ነው::

በሀገሪቱ ዳር እስከዳር አባላትን ያፈራ 8 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን በአባልነት ያቀፈ ግዙፍ ፓርቲ ነው:: የሰራቸውን ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ስራዎች በምንም ተአምር መካድ አይቻልም:: ዛሬም ስህተቶቹን አርሞ አደረጃጀቱን ለውጦ ከግንባርነት ወደ አንድ ብሔራዊ ፓርቲነት ተለውጦ፤ ሁሉን አቀፍ የፖለቲካ መድረክ ከፍቶ አሳታፊ በመሆን ሌሎችም በዜግነታቸው መሳተፍ የሚችሉበትን እድል አስፍቶ

ሁሉም በጋራ ሀገሩን እንዲያለማ ሰላሚን እንዲጠብቅ በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ወደ ፖለቲካ ስልጣን የመምጣት ባሕል እያደገ እየጎለበተ እንዲሄድ ዛሬም ከነችግሮቹ ምርጫችን ኢሕአዴግ ብቻ ነው፡፡

በትርምስና በሁከት ሀገር ለማፍረስ የሚክለፈለፉት ሺህ ቦታ የተከፋፈሉ ፓርቲዎች ድርጅቶች ሰፊ ሀግን ለመምራትም ለማስተደደርም አይመጥኑም፡፡ የጋራ የሚባል አላማና ግብ የላቸውም፡፡ በአስተሳሰብ የማይግባቡ እርስ በእርስ የሚናቆሩና የሚባሉ ፓርቲዎች ይህችን ሀገር ወዴት እንደሚወስዷትቡ መተማመኛ የለውም፡፡ የማይታወቁ በበቀልና በጥላቻ የተሞሉ የረባ የሚታይ አደረጃጀትና የፖለቲካ መስር የሌላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሀገርን አደራና ኃላፊነት ተረክበው የመምራት የማስተዳደር አቅሙም አደረጃጀቱም የላቸውም፡፡

አይደለም ሀገር ሊመሩ እራሳቸውንም በቅጡ መምራት የሚችሉ አይደሉም፡፡በጥላቻ በበቀል ፖለቲካ ተዘፍቀው ከማጓራት ያለፈ ሀገርን በሰላም በማረጋጋት ሊመሩ የሚችሉበት ቁመናየ የላቸውም፡፡ ገና ከእብደት ፖለቲካቸው አልተላቀቁም፡፡ ለግብጽ ለኤርትራ በቅጥረኝነት ያደሩ ሎሌዎች እንደነጀዋር በሚሊዮኖች ከግብጽ በጀት ተመድቦለት እስላማዊ አክራሪነትን በኦሮሞ ሕዘብ ስም ለሚያቀነቅን ቅጥረኛ የአልሻባብና የአይሲስ ተላላኪና መሰሎቹ ኢትዮጵያን በግርግር አሳልፎ የሚሰጥ ማንም የለም፡፡

ባለሜንጫው ጀዋር ስልቱን እየቀያየረ በሚረጨው መርዝ የኦሮሞ ወጣቶችን በማታለል ለከፋ አደጋ አጋልጦ የሰጠ በታሪክና በትውልድ ተጠያቂ መሆኑም መታወቅ አለበት፡፡ በኦሮሚያ ለደረሰው ጥፋትና የሀገር ንብረት መውደም የጎሳ ግጭት የዜጎች ሞትና መፈናቀል ዋነኛ ተጠያቂው የአክራሪው እስላማዊ ኃይል ተቀጣሪና የእምነቱ አራማጅ የሆነው የሚቃወሙትን ሁሉ አንገታቸውን በሜንጫ እንቀላዋለን በማለት ስምሪት ሲሰጥ የነበረው ጃዋር መሀመድ ነው፡፡

በፍቅር በሰላም ተከባብሮ ተቻችሎ ለዘመናት የኖረውን ሕዝብ እርስ በእርስ በማባላት የጥፋት አጀንዳ የሚያራምዱትን ወገኖች አጀንዳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሕሉም እምነቱም ስለማይፈቅድና ስለማይቀበል አንቅሮ ይተፋቸዋል፡፡ የሰከሩና ያበዱ ፖለቲከኞች ሀገርና ሕዝብን በማውደም ደም በማፋሰስ የፖለቲካ ስልጣን እንይዛለን የሚለው እብደታቸው ከንቱ ከከንቱም ከንቱ ነው፡፡ እናም፤ ረጋ ብሎ ማሰብ፤ ማስተዋልን ልብ ሊሉት ይገባል።

ወጣቶቻችንም ይህ ዘመን አመጣሹ ማህበራዊ ሚዲያ ህብረተሰቡን ከማገልገል፣ ሰላምን ከማስፈን፣ ልማትን ከማፋጠን፣ መቻቻልን ከማስተማር፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ከማጎልበት በተቃራኒ በመሆን ምን ያህል ፀረ-ማህበረሰብ እየሆነ እንደሆነ መመልከትና ወደሰላማዊ ህይወት እንቅስቃሴያቸው መመለስ ይጠበቅባቸዋል።